# አውቀን አንድ እንሁን

በአሻን መንገድ ተጉዘን ትልም አውጥተን መዳረሻ፣
በብልህነት ባሳብ በዝተን ግቡን አውቀን መጨረሻ።
እንደ ቀስተ ደመና ደምቀን ተውበን በህብረ ቀለማት፣
ልዩነታችንን ጌጥ አድርገን አንድነታችን ሆኖን ጉልበት፤
ሩቅ እናልም በብልሀት ሰላም ብልጽግና ወዳለበት።
አፍንጫ ስር ካለው ከተልፈሰፈሰው ጠላታችን ልቆ፣
ይበጀን እንጂ ማየት ማስተዋል መድረሻውንም ጠንቅቆ።
ባጠፉ መጠን ሞቱን ሲያፈጥን መቀበርያውንም ምሶ፣
ወያኔማ ባንጥለውም ይወድቃል የዘመን ዑደቱን ጨርሶ።
እርስ በርስ ስንጓተት ሆነን እንዳንቀር የአለም ጭራ፣
አውቀን አንድ እንሁን ነቅተንም በጋራ እንስራ።

ክብር መውደዳችን ባልጣማቸው ኩራታችንን በሚፈሩ፣
ወደ ሽፍታ አዙሪት ያስገቡን ከንጉሱም ወደ ወታደሩ።
ከእምዬ ጉያ ከነጠሉን የሚስሙ መስለው ከሚነክሱ፣
ዘራችንን በዓለም ዘርተው ሀገራችንን ቁልቁል ያሳነሱ ።
በ «ኒው ወርልድ ኦርደር» አዲሱ የአገዛዝ ምርጫ፣
ሊሸነሽኑን የተማማሉ በ «ማኔጀብል ሳይዝ» ቅርጫ።
እኒያን ሁሉ ካልመዘንን ካልገባን የብልህነት መንገዱ፣
ታሪካችንን ከተረት ጀግንነታችንን ከጅልነት እያዋሀዱ።
ኩራት አልባና ጥገኛ፣ አንገት ደፊነት ይሆናልና ግዱ፣
አለማዊ እውነታውን አገናዝበን ካገራዊ ሁኔታም አጣጥመን፣
በነቃ የአስተሳሰብ መንገድ እንሂድ ሳይነጋ እንዳይጨልምብን።

ጀግና ነን ብለን ስንፎክር ተጭኖን የፍርሀት ቀንበር፣
አዋቂ ነን ብለን ስንመጻደቅ በአለማወቃችን ታዛ ስር።
አንድ ባንድ ቀን በቀን እያነሰን በአንገታችን ሲጠልቅ ማነቆ፣
አልሄድ ባልን ነውና ሰቆቃው አላማና ግቡ በውል ታውቆ።
አንድ ሆነን ስላልጣሉን ያሴሩብን ሊያሳንሱን በሸንሸና፣
አልተኙም አላሸለቡም ለዘመናት መቼ የሚሹት ደረሰና።
የተሸነፉ ጣልያኖችም ያን መከሩ  ጀርመኖችም ተቀበሉ፣
የአሜሪካ የመግዛት አባዜም ያው ነው አረቦቹም ተማማሉ።
ያገሬ ልጅ ጥበብ ሰንቅ ታሪክ እወቅ ጠላትህን ለይ በየፈርጁ፣
የጎሳ መሪዎችማ ተላላኪ ናቸው  ቅጥረኛ ለአረቡ  ለፈረንጁ።
ያወቁም ከመሰላቸው ስህተት አውቀው ከሆነም ከሀዲዎች፣
በነርሱ ጉያ ገብተን የኢትዮጵያችንን መበተን አናመቻች።
በማነስ ከነገሰው ከእብሪተኛው ከኢሳይያስ ከንቱነት እንማር፣
አገር ሻጩን ወንበዴ ቅጥረኛው መለስን አይተን እንመከር።

እንዳላወቁ ሁሉ እንዳናልቅ ሳናይ የእለት የእለቱን ብቻ፣
በእንዲህ ባረግን ጸጸት ዛሬ አምልጦን ነገን ሳንሆን መዛበቻ።
በሆይ ሆይ የሚወጣ ሁዋላም በዋይ ዋይ የሚመለስ፣
የትውልድ ከንቱ እንዳንሆን የሰራውን የሚያፈርስ።
በ «ያገባኛል ትግል» እንግባ በ«ይገባኛል ነጻነት» እንነሳ፣
በ ተናጠልም ይሁን በህብረት የነጻነት ሰንደቅ እናንሳ።
እናም እንደ ቀስተ ደመና ደምቀን ተውበን በህብረ ቀለማት፣
ልዩነታችንን ጌጥ አድርገን አንድነታችን ሆኖን ጉልበት፤
ሩቅ እናልም በብልሀት ሰላም ብልጽግና ወዳለበት።

በትንሣዔ

ሰኔ 2008